# የዋልድባ መነኮሳት ሳይፈቱ መቅረት የወያኔን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጠላትነትን የሚያረጋግጥ ነው ።

February 27, 2018

ከቀሲስ አስተርአየ ጽጌ

በፖለቲካ መርኃ ግብሩ ላይ በግልጽ እንዳስቀመጠው ለተነሳበት ኢትዮጵያን የማጥፋትና በጎሳ ለያይቶና አዳክሞ የመግዛት ፖሊሲ አማራውና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እንደ ታላቅ ጠላት ተቆጥረው እንዲወድሙ እወያኔ ንደወሰነባቸው ይታወቃል። ወያኔ ይህንን መሠረት በማድረግ ቤተክርስቲያኒቷ ላይ ሁልቆ መሳፍርት የሌለው በደልና መከራ አድርሶባታል። በዚህ መሠረት የጥቃት ኢላማ ከሆኑት የቤተክርስቲያኒቷ አውዶች ታላቅና አንጋፋው የዋልድባ ገዳም ይገኝበታል።

የዋልድባ መነኮሳትና መናንያን በዕምነታቸው ጽናት ምክንያት ይህንን ዓለም ንቀውና ተጸይፈው ህዝብ ከሚኖርበት መንደር እጅግ ርቀው ጫካና ዱሩን ቤታቸው አድርገው፣ ግርማ ሌሊትን ድመጸ አራዊትን ታግሰው፣ ጤዛ ለብሰው ዳዋ ተንተርሰው ለዘመናት ይኖሩ ከነበረበት ገዳማቸው ተነቅለው በኢጋዚ ወታደሮች ጥይት እየተተኮሰባቸው ወደ እስር ቤት መጋዛቸው ይታወቃል። ይህ አይደፈሬ ገዳም እንኳንስ በኢትዮጵያ መንግሥታት ሊነካ ይቅርና በጣሊያን ወራሪዎችና አገር አጥፊዎች አንኳ ሳይደፈር የቀረ ሲሆን በዘመናችን ጥቁር ሙሶሎኒዎች ህወሃቶች ግን ረክሰና ተዋርዶ የመናንያንና መነኮሳት መካነ መቃብሮች በግሬደር እየታረሱ አጽማቸው እንደ ቆሻሻ ሲጣል መመልከት ከዘመናችን አስከፊ መከራዎች አንዱ ነው። የገዳሙ ይዞታና ንብረት የሆነውን መሬት ካልጠፋ ቦታ “ለሸንኮራ አገዳ ማብቀያ” በሚል ሰበብ ለህወሃት ጋሻጃግሬዎች ታደሏል።

መነኮሳቱም በገዳማቸው ላይ የደረሰውን ውድመት አምረው በመቃወማቸው ምክንያት ብዙዎቹ ለእስር እንዲዳረጉና ክብራቸው እንዲዋረድና ስነልቦናቸው እንዲጎዳ ከዚህ ዓለም በሞት እስኪለዩ ድረስ ሊያወልቁት የሚይፈቀድላቸውን የምንኩስና ልብሳቸውን እንዲያወልቁ በኢጋዚ ወታደሮች ከፍተኛ እንግልት ደርሶባቸዋል። ህገ መንግሥትና የኅይማኖት ነጻነት አለባት በምትባለው አገር ውስጥ በተለይም ከ 2000 ዓመታት በላይ በአገሪቱ ውስጥ እጅግ ከፍተኛ አስተዋጽኦና ለአገሪቱም አለኝታና መከታ የሆነችው ኦርቶዶክስ ተወህዶ ቤተክርስቲያን ላይ ተዘመተባት። በፓትርያርክ መንበር ላይ በወያኔ የተቀመጡት ያለፉትና አሁንም ያሉት ሁለቱም ፓትርያርኮች የጎሳ ልክፍት የተጸናወታቸው ስለሆነ ለመንጋው የማይጨነቁና ከአራጆች ጋር አብረው ህዝብ ላይ ካራ የሚሰነዝሩ ሆነዋል። የሲኖዶስ ጉባዔ ላይ የሚታደሙት ጳጳሳትም በአብዛኛው ነፍሳቸውን ትተው ለስጋቸው ያደሩ ስለሆነ የቤተክርስቱያንና የአገር ነገር ግድ አይሰጣቸውም። እንደ አቡነ ፋኑኤል (አባ መላኩ) ዓይነት የከተማ ጩሉሌዎች በገንዘብ ጭምር ጽጽስና ማግኘታቸው በጉባኤ እየተነገረ ምንም ዓይነት የእርምት እርምጃ አልተወሰደባቸውም። በመሆኑም እነሱ በቤተክርስቲያን ላይ ለሚደርሰው ውድመት ይደልዎ የሚሉ እንጅ የሚቃወሙ አልሆኑም ባህርያቸውና ማንነታቸው አይፈቅድላቸውምና።

ወያኔ የቤተክርስቲያኒቷን ነጻነት በመዳፈርና በትዕቢት በሲኖዶስ ጉባኤ ላይ ጭምር ከቀኖና ቤተክርስቲያን ውጭ ካድሬዎቹን በማቀመጥ ንቀቱንና ጥላቻውን ከማሳየቱም በላይ ልብሰ ተክህኖ እያስለበሰና መስቀስ እያስጨበጠ አሰርጎ ያስገባቸው ሰላዮቹ ቤተክርስቲያኗን እየገዘገዟት ነው። ህብረተሰቡ ይህችን የልቡ ትርታ የሆነች ቤተክርስቲያን እንዲሸሻትና እንዲተዋት በዝሙትና በሙስና የተጨማለቁ ወንበዴዎችንና ማጅራት መችዎችን የካህናት መታወቂያ እየሰጠ በየቤተክርስቲያኑ በመደልደል ከፍተኛ የስነምግባር ሰለባ ዘመቻ በማካሄድ ላይ ይገኛል።

ወያኔ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ የፖለቲካ እስረኞችን እያሰቃየ እንዳለ የሚታወቅ ሲሆን፤ ሰሞኑን በህዝባዊ ተቃውሞ ምክንያት ብርክ ስለያዘውና ሲቃ ውስጥ በመግባቱ በግድ ታዋቂ የፖለቲካ እስረኞችን ፈቷል። ሆኖም ለብዙ ዓመታት በግፍ እስር ቤት የሚያንገላታቸውን የዋልድባ መነኮሳትን ግን አልፈታም።ይህም የሚያሳየው ወያኔ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ

ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን እንደ ደበኛ ጠላት እንደሚመለከታት ነው። የነዚህን መነኮሳት አለመፈታት መቼም ከአሳሪዎቹ ጎን የቆሙትና የትግራይ የበላይነት አጋፋሪ የሆኑት አቡነ ማቲያስ ያሳስባቸዋል ብሎ ማሰብ ከእብደት አይለይም።ሆኖም በውጭ የሚገኘው ሲኖዶስም ስም ብቻ ሆኖ መቅረቱን የሚያረጋግጠው በእንደዚህ ዓይነት አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ ካልተወተወተና ካልተገፋ በራሱ አነሳሽነት ወቅቱ የሚጠብቀውን ተግባር መፈጸም ተስኖታል። ይህች ከ 50 ሚሊዮን በላይ አማኞች ያሏት ጥንታዊት ቤተክርስቲያን ምንም እንኳ በ 2000 ዓመታት ታሪኳ ውስጥ እጅግ ከፍተኛ ከውጭ የመጡባትን ተግዳሮቶች ስትቋቋምና ስትረታ ብትኖርም ይኸኛው ፈተናዋ የደረሰባት ከራሷ አብራክ በወጡ ጡት ነካሽ ልጆቿ በመሆኑ ቁስሏ በቀላሉ የሚሽር አይመስልም። በዚህ ፈታኝና የሰው ያለህ በሚባልበት ጊዜ ቤተክርስቲያኒቷ የሚጮሁላት ጥቂት አባቶችን አላጣችም። ከነዚህም መካከል አንዱ የሆኑት ሳይታክቱና ሳያሰልሱ ለቤተክርስቲያንና ለአገር አንድነት ድምጻቸውን የሚያሰሙት አንጋፋው አባት ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ የዋልድባ መነኮሳት በእስር አለመፈታታቸውን አስመልክተው ያስተላለፉትን መልዕክት አቅርበንላችኋል።

https://www.youtube.com/watch?v=79MtGaB26Hc